# ኧረ ስለደንብ..... በደንብ አምላክ

(በህያዉ ቃል )

እንዲህ እንደዛሬ ሁሉ ነገር ከመበለሻሸቱ በፊት ከባህልና ከማህበራዊ ልማዶቻችን መንጭተዉ የተዋሃዱንና የኑሮ መርህ ያደረግናቸዉ አያሌ ደንቦች ነበሩን ። እንደብርቅ እንስሳት በመጥፋትና በመመናመን ላይ ቢሆኑም ዛሬም አሉን ።ደንቦቹ አንቀጽ የማይጠቀስላቸዉና ያልተጻፉ የመሆናቸዉን ያህል ለአፈጻጸማቸዉ ክትትል ፖሊስም ሆነ ዐቃቤ ህግ የማይሹ ነበሩ ። አስከባሪ አላቸዉ ቢባል እንኳ የፈጠራቸዉና በዉስጥ ስምምነትም ያጸደቃቸዉ ማህበረሰብ ብቻ ነዉ። ብዙዉን ጊዜ ደንቦቹን ሲተላለፉ የሚታዩት አቅላቸዉን የሳቱ ፤ በዘልማድ ወፈፌ በሚል ቅጽል ስም የሚታወቁ ሰዎች ናቸዉ። ኣዕምሮዉ የተቃወሰ ሰዉ ደግሞ ቢያስቸግር ለጥቂት ጊዜ፤ ያዉም በዘመድ ርብርብ ወይም በወጠምሻዎች ጉልበትተይዞ  ወደ ጸበል ካልሆነም ወደ አማኑኤል እስኪወሰድ ድረስ ነዉ ።

ጥቂት ዓመታት ወደኋላ መለስ ብለን ተወልደን ያደግንበትን ወግና ልማድ ብናጤን ይህንኑ የሀገርና የደንብ ጥብቅ ትስስር እናስተዉላለን። የኢትዮጵያ ሕዝብ ለሀገሩና ለነጻነቱ ያለዉ ፍቅርና ቀናዒነት እጅግ ከፍተኛ የመሆኑ እዉነትነት በፍጹም የሚያጠራጥር  አይደለም። የፍቅሩን ጽናት ያህል ሀገሩን በወላጅ እናት ተምሳሌ “ እማማ “ ብሎ ነዉ በቁልምጫ የሚጠራት ። በከፋዉ ጊዜ እንኳ ይህን ቁልምጫዉን አይነፍጋትም ።ገዥዎቹ ሳይቀሩ ለተጋድሎ ክተት ሲሉት  በ”እማማ” ስም አዉጀዉ ነዉ የሚጠሩት ። ጥሪያቸዉን ሰምቶም አያወላዳም፤ ክፉዋን ለመመከት ኑሮዉን በትኖ ታጥቆ ወጥቶ ያድርላታል -ይቆስል- ይደማላታል ፤ ይሞትላታልም ።ከዚህ መሰረታዊ እዉነታ በመነሳትም ያልተጻፈዉ ማህበረሰባዊ ደንብ አያሌ ትዉልዶች ወጥተዉ የወረዱላትንና የሞቱላትን ሀገር -ኢትዮጵያን በይፋ ማንወርን ሆነ ክብሯንና ታሪኳን ማንኳሰስን  አጥብቆ ይኮንናል። ጭርሱኑ ለይቶለት ጨርቁን የጣለ እብድ ካልሆነ በቀር የሀገርን ክፉ ርዕሰ ጉዳይ አድርጎ በአደባባይ አፉን የሚያላዉስ  ጤነኛ ኢትዮጵያዊ የለም ። የኢትዮጵያ ታሪክ ፤ ክብር ፤ነጻነቷና አንድነቷ አይነኬ ከሚባሉት ጉዳዮች አቢዩ ሆኖ ቆይቷል። ለብዙዎቻችን ዛሬም አይነኬ ነዉ።

“መሬት ሲያረጅ መጭ ያበቅላል” ይሉ ነበር አባቶች። ለዘመናት ግፈኛ ስርዓቶችንና ድህነትን በጫንቃዉ ተሸክሞ የኖረ ዕድሜ ጠገብ አገር ምን እንደሚያበቅል አይታወቅም። ነገር ግን ጨርቃቸዉን ያልጣሉ የአገር ደንብ ሰባሪዎችን በዕዉናችን እያስተዋልን ነዉ። ከዚያችዉ ሀገር መብቀላቸዉን የማይክዱ ወገኖች ዘመኑ ያፈራቸዉን የመገናኛ ዘዴዎችና የስብሰባ መድረኮች በመጠቀም በተከታታይ ትዉልዶች መስዋዕት በተገነባዉ የኢትዮጵያ ክብርና አንድነት ላይ ሲዘባበቱና ከምንም ነገር በላይ ከፍ አድርገን የምናያቸዉን ብሔራዊ እሴቶች ሲያጣጥሉ ይዉላሉ ፤ ያድራሉም።

እርግጥ ነዉ እስከ አሁን ያለዉ ጥረታቸዉ ከዲስኩርና ከወሬ ያላለፈ በመሆኑ እንቅልፍ አጥተን የምናድርበት ጉዳይ አይመስል ይሆናል። ሆኖም ግና ከእነዚህ ወገኖች የሚሰማዉ ጫጫታ ለዴሞክራሲና ለፍትሀዊ ስርዓት ከሚደረግ ትግል ጋር ተያይዞ የሚደመጥ በመሆኑና ዞሮ ዞሮ የሚያጠነጥንበት ዉልም ከእንገንጠል ባይ ሀይሎችና ከአይዞህ ባይ አስታጣቂዎቻቸዉ ጋር የመተዛዘልን አስፈላጊነት የሚሰብክ ነዉና ስር ከመስደዱና በቀላሉ የማያጠፉት አቀንጭራ ሆኖ ከመጋረጡ በፊት ከዘላቂዉ የሀገር ጥቅም አንጻር ሊፈተሽና አቀንቃኞቹ ክፍሎች ከወዲሁ ሀይ ሊባሉ ይገባል ።

ትግልና የዋህነት አብረዉ አይጓዙም ።ብሶታችንን እያቀነቀነ ከበሮ ለሚደልቅ ሁሉ "አይፈራም ጋሜ " በሚል ትከሻችንን ለማርገፍገፍ ከመነሳታችን በፊት ከዉስጥ ነብሳችን ለሚመነጭ የታማኝነት ጥያቄ ርግጠኛዉን መልስ ልናገኝለት ይገባል።ሰዉዬዉ " ጅልን እባብ ሁለቴ ይነድፈዋል ፤" ቢሉት "ያዉም በጊዜ ከነቃ፤" አላቸዉ ይባላል ።በጊዜ ያልነቃ ወገን መቁጠር እስኪያታክተዉ ድረስ ለተደጋጋሚ ጥቃት ሰለባ መሆኑ አይቀርም።

በጸረ -ወያኔነትና በዴሞክራሲ ስም መሃላ ደርድሮ መሀከላችን የተደነበ ሁሉ በጥቅሉ ጸረ-ወያኔም ዴሞክራትም አለመሆኑን ቢያንስ የተሰጣቸዉን ተልዕኮ ከፈጸሙ በኋላ ወደላካቸዉ ካምፕ በይፋ ከተቀላቀሉት ባለ "ሶስተኛ መስመር " ቀጣፊዎች ድርጊት ተምረናል ።ዛሬም ቢሆን የመመለሻ ቀናቸዉን የሚጠባበቁ ሌሎች መሰል ተሹለክላኪዎች በመሀከላችን የሉም በሚል ርግጠኛ ሆነን መወራረድ አንችልም ። ወያኔ እንደሁ ዘብጥያ አዉርዶ የሚመልሳቸዉን አገልጋዮቹን ወደሚፈራዉ የሕዝብ ሰልፍ ልኮ መቀየጥን ሰይጥኖበታል።

እንደሚታወቀዉ የወያኔን " ምርጫ " ታክኮ የተቀሰቀሰዉ ሕዝባዊ የለዉጥ ማዕበል በሀይልም በሸፍጥም እንዲመክን ከተደረገ ወዲህ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ሀይሎች መሀከል አዲስ መሳሳብና መሻኮት ተከስቷል ። አንድ ወቅት በጋራ ቆመዉ የነበሩ ቡድኖች ተሰናጥረዋል። የዚያኑ ያህልም አንድ በባህሪዉ ያልተለመደ ግንጠላን ግባቸዉ ያደረጉ ተስፈንጣሪ ቡድኖች የተካተቱበት "የትብብር አካል" ተፈጠረ ተብሎም ብዙ ተለፍፏል።ሆኖም በወቅቱ የትብብሩ አባላት በዓላማ ግቦቻቸዉ ረገድ ርስበርስ ተገዳዳፊ መሆናቸዉና በመስራች ጉባዔያቸዉ መማከያ ምርጫ ላይ የአገሪቱን የስራ ቋንቋ አስወግደዉ በባዕድ ቋንቋ የተጠቀሙ መሆኑ በመሰማቱ የብዙ አገር ወዳዶችን ቁጣ ቀሰቀሰ። በዚህም ሳቢያ ብዙ የተጨበጨበለቱ ትብብር ዕድሜም ሳያስቆጥር በአጭር ቀረ ፤ ወይም ባጭር የቀረ መሰለ።

ትብብሩ ያስነሳዉ ጩኸት ገና ከማባራቱ ከእስራት ወደስደት የሚመጡት የተበታኙ ቅንጅት ዉህድ አንድ ክፍል መሪ የነበሩት ዶክተር ከዚያ ቀደም በኋላቀርነት ሲኮንኑት የቆዩትን የሁለገብ የትግል ስልት ሁነኛ ስልታቸዉ አድርገዉ አዲስ ድርጅት ይዘዉ ብቅ ይላሉ። ይህ አዲሱ አቋማቸዉ በታወጀበት ሰዓት ብዙም አላስደመመም። ቀድሞ ነገር ወያኔን የመሰለ አምባገነናዊ አገዛዝ በሰላማዊ መንገድ ይወገዳል የሚለዉን አስተምህሮአቸዉን ከልብ ያልተቀበለላቸዉ ወገን " ገና አሁን ከምር ትግል ሜዳ ገቡ ፤" በሚል " አበጀህ ሊላቸዉ ቋመጠ። ሆኖም በዚህ ጉጉትና የትግል ሙቅ ስሜት ላይ በራድ ዉሀ ለመከልበስ ዶክተሩና ፈጠርኩት ያሉት ስብስብ ጊዜ አልፈጀባቸዉም ።( ዶክተሩ በወቅቱ ከዚያ ቀደም ከቅንጅት መሪነታቸዉ ጋር በተያያዘ ከገቡበት የሕዝብ ጥርጣሬ አዘቅት ዉስጥ ገና ሙሉ በሙሉ ስለመዉጣታቸዉ እንኳን

ርግጠኛ አልነበሩም።ሰዉዬዉ በግንቦቱ ምርጫ  የሕዝብን ድምጽ ለማስከበር የተጠራዉን ሕዝባዊ አመጽ በማክሸፉ ሴራ እጃቸዉ አለበት መባሉንና ከዚያም በፊት ከወያኔ ጋር የታሙበትን ሽርክና ልብ ይሏል ።)

ብዙም አልከረመ ፤ አዲሱ ድርጅት ወያኔአዊዉን አገዛዝ ለማስወገድ ከኤርትራዉ አገዛዝ ጋር ተባብሮ እንደሚሰራ ግልጽ አደረገ ። በዚህም መሰረት መሪዎቹ ከገዢዉ የሻዕቢያ ቡድን ቡራኬ ለማግኘት በተደጋጋሚ ወደ አስመራ ከተማ አቅንተዋል ።ይህን መሰሉ ግንኙነት ዉሎ አድሮ ሊያስከትለዉ የሚችለዉ ተጽዕኖ ወይም ፖለቲካዊ የእጅ ጥምዘዛ ሊኖር የመቻሉ ጉዳይ ከየዋሀን አባላቱ ዘንድ እንጂ ከሌሎቹ የተሰወረ አልነበረም።ከሻዕቢያዉ ኢሳያስ አፈወርቂ ፊት ሞገስ ለማግኘት ሲባል ቢያንስ ሰሜናይቱ ተገንጣይ ግዛት ከጉያዋ ያስጠጋቻቸዉን ቡድኖች ተቀብሎ አብሮ መስራት የግድ ይሆንባቸዋል የሚል ግምትና ስጋት በብዙዎቹ ተመልካቾች ህሊና ሲጉላላ ሰንብቷል ። ያ ስጋት ግን ወድያዉኑ ከግምታዊነት አልፎ ዕዉን ሆኗል ።ይኸዉ እስከዛሬ “ሕብረትን ፍለጋ” የሚል ዉብ አገራዊ ዕቅድ ተላብሶ  በየቦታዉ ከእንነጠል ባይ ቡድኖች ጋር ስብሰባዎች መቀመጥ የድርጅት ስራ ሆኖአቸዉ ከርሟል ። “ሕብረት ለምን ፤ ከነማንስ ጋር ?” በሚል ከታዛቢ ለሚነሳባቸዉ ጥያቄ የሚሰጡት መልስ የተዉገረገረ ከመሆን አልፎ ተገንጣዮቹ አቋማቸዉን ቀይረዉ ለአገር አንድነት ለመታገል መነሳታቸዉን በሚገልጽ ሀሰተኛ ዘገባ ላይ የተመሰረተ ነዉ። ይህንን፤ ገና ያልተፈለፈሉ ጫጩቶቹን ከሚቆጥር የዋህ የዶሮ አርቢ ጋር የሚያመሳስላቸዉን ሁኔታ ነዉ እንግዲህ ዶክተሩና መሰሎቹ ከዚህ ቀደም ያልታዬ ቅንብር (ፓራዳይም ሺፍት ) እያሉ በማቆላመጥ የሚጠሩት  ። (ይህቺ የፈረንጅኛ ሐረግ ደግሞ አዲሳችን አይደለችም ፤ ከቅንጅት ( ማፍረሻ?) አለማቀፋዊ ማስተባበርያ (ኪል )ጊዜ አንስቶ ስትንከባለል የከረመች ኩምክና ናት፦ ኮማኪዎቹም አልተቀየሩላት።)

ከላይ የተመለከቱትን ሀሳቦች በሚጠቀልላቸዉ አንድ ሀይለቃል  ብናስቀምጣቸዉ ” የሕዝቦች እኩልነትና ፍትህ የሰፈነባትን ዴሞክራስያዊት ኢትዮጵያ በሻዕቢያ ትብብርና በተገንጣዮች ሕብረት እዉን እናደርጋለን ” ከሚል መፈክር የዘለለ ምንም አናገኝም ።ከራስ ሐሳብ ጋር መጣረስ ማለት ይህ ካልሆነ ሌላ ምን ሊሆን ይችላል ?....ከዚህ በላይስ የሀገርን ደንብ እንደምን ይጥሷል?

ይህ አቋም ብዙም እንደማያፈናፍናቸዉ አያዉቁትም ማለት ዶክተሩንና መሰሎቻቸዉን ዝቅ አድርጎ መገመት ይሆንብናል ፤ ቢያንስ በአጭር ዕድሜዉ ከተቀጨዉ ትብብር ቁ.1 ትምህርት አልገበዩም ማለት ይመስላል።ስብሰባዎቻቸዉን ልብ በሉ። ብዙዉን ጊዜ የሕዝብ ከበሬታ ባተረፈና በአገሩ ፍቅር በነደደ ከያኒ የመግቢያ ንግግር ነዉ የሚከፈቱት።ይህ በራሱ መራራዉንና መርዛማዉን ጉዳይ በማር ጠቅልሎ የማስዋጥን የረቀቀ ዘዴ (ሐያስያኑ መሰሪነት ይሏታል) አያመለክትምን?..ጥፋቱን ያላወቀ.የዋህ ይህን ያህል ድብብቆሽ አይጫወትም።

የዚያኑ ያህልም ዲስኩራቸዉና ተግባራቸዉ ከመጋባታቸዉ በፊት የተፋቱ ናቸዉ። “ሕብረት” ይሉናል። “አገርን ማዳን” ይሉናል። በአፋራሹ፤በኢትዮጵያ አንድነት የማያወላዉል አቋም ካላቸዉ የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር ለመቀራረብ ከመጣር ይልቅ ከሀገሪቱ መገንጠልን ዓላማቸዉ አድርገዉ  የሚታገሉ ወገኖችን ለማሸኮርመም ጊዜአቸዉን ሲፈጁ እናያቸዋለን። ይህም ከጅምሩም ከአንድነት ሀይሎች ጋር የመስራት ዉጥን አልነበራቸዉም የሚለዉን አሉታዊ ግምት ለእዉነት የቀረበ ያደርገዋል ።

ተባብረዉ ለመስራት ይህን ያህል ቀና ደፋ የሚሉላቸዉ ወገኖች ደግሞ በአገር ቤት ነፍጥ አንስተዉ የታገሉና የሚታገሉ መሆናቸዉ ሌላም የሚያመላክተዉ ነገር አያጣም። "ይህቺ ሳር አጨዳ ዱባ ፍለጋ ነች " እንዲሉ የአራዳ ልጆች ፤ዶክተሩ ያለብዙ ልፋት ወደ አራት ኪሎዉ የስልጣን መንበር ለመጋለብ መዘየዳቸዉን የሚገምቱ በርካቶች ናቸዉ። ማን ጋላቢ ማንስ ተጋላቢ እንደሚሆን ከወዲሁ ተለይቶ የታወቀ ነገር አልተገኘም ። ዶክተሩ ዕድል ቀንቶአቸዉ ጋላቢ ለመሆን ቢበቁ እንኳ አገር አቋራጭ የጋለቡበትን ነፍጠኛ ፈረስ እንደምን ወደመስከ ሊያሰማሩት እንደሚችሉ ከወዲሁ ያሰቡበት አይመስሉም፤ ( ከሕዝብ ደብቀዉ የያዙት አንዳች ተዐምር ከሌለ በስተቀር።)

በሻዕቢያ አዋላጅነት ኢትዮጵያ ዉስጥ ለልደት የሚበቃ አንዳችም በጎ ነገር አለመኖሩን ጨምሮ መገንጠልን በመርህ ግብራቸዉ ካካተቱ ወገኖች ጋር የሚፈረም ሕብረት ጣጠኛ ስለመሆኑ ከሕዝብ በግልጽ ለሚነገራቸዉ ስጋት ማስታገሻ ፈዉስ የላቸዉም።በምትኩ "ማየት ያለባችሁ ዋናዉን ዓላማ (የወያኔን መገርሰስ ) ነዉ "በሚል አባባል ሊያጃጅሉን ይቃጣቸዋል።አባባሉ ሳሩን እንጂ ገደሉን ያላስተዋለዉን ተረታዊ በሬ ብቻ ሳይሆን እንደ ሕዝብና እንደ ሀገር ያለፍንበትን እዉነታ መለስ ብለን እንድናስታዉስ ያስገድደናል። "ወታደራዊዉ አገዛዝ ይዉደቅ እንጂ......'' ብሎ ከምኞት አድማስ ላይ ዐይኖቹን ያቁለጨለጨ ሕዝብና ሀገር በመካያዉ የተረፈዉ ደርግ በተገረሰሰ ማግስት የወያኔን ዛዝላ ከጫንቃዉ አዉጥቶ መጎተት መሆኑን ዶክተሩና ስብስባቸዉ እንዴት እንደዘነጉት የሚገርም ነዉ።ባለ ነፍጡ ወያኔ ተከዜን መሻገር ሲያስብ እነማንን በመጋዣ ፈረስነት ለጉሞ እንደነዳና ምኒልክ ቤተመንግስት ከደረሰ በኋላ ደግሞ ምን እንዳደረጋቸዉ የኢትዮጵያ ሕዝብ አበጥሮ ያዉቃል።

ከዚያዉ እኩል ሕብረት ስለሕብረትነቱ ብቻ ሲባል የሚፈለግ አለመሆኑን አሳምሮ ያዉቃል። ሕብረት የጋራ ትግልንና ጥረትን ማቀናጃ መሳሪያ መሆኑንም ይገነዘባል ።በአምስት ዓመታቱ የነጻነት ተጋድሎዉ ወቅት የጸረ ፋሽስት ህብረትን ተገን አድርጎ በሚወዳት አገሩ ላይ ድብቅ ሴራ ሲጎነጉን የነበረዉን የእንግሊዞች መሰሪነት ያከሸፈ ታላቅ ሕዝብ ይህ ዕዉቀቱ በማንም ዘንድ ኮስሶ ሊታይ አይገባዉም ። አነሳሳችን በርግጡ ዘለቄታዉ ላማረ ሕብረት ከሆነ እስቲ በቅድሚያ በአንድነት ሀይሎች መሀከል ይጀመር።ገንጣዮቹም አቋም መቀየራቸዉን በይፋ እያስታወቁ መጥተዉ ይቀላቀሉ ። እሳማለሁ ብለዉ ከማያምኑት ዘንዳ ሲሄዱ ተነክሶ መመለስም መኖሩን አለመዘንጋት ብልህት ነዉ።